2) በኢትዮጵያ፥ ለኦርቶዶክስ ክርስቲያኖችና ለሌሎችም የግርዘት ዓላማ ምንድነው?

3) ሴቶች የሚገረዙት ለምንድነው?

4) ስለ ሴቶችና ወንዶች ግርዘት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማስተማር የሚገባን ምንድነው?

5) ግርዘት ከጥምቀትና ከቅዱስ ቁርባን ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

6) በዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የጥምቀትና የቅዱስ ቁርባን ዓላማ ምንድነው?

ሠ. 1) የሎጥን ውድቀት ዛሬ ከሚታየው የብዙ ክርስቲያኖች ውድቀት ጋር አወዳድር። የሚመስሉት ወይም የሚለያዩት እንዴት ነው?

2) ሎጥ እንዳደረገው፥ ክርስቲያኖች በኃጢአት እንዳይወድቁ ለማስጠንቀቅ፥ በአብያተ ክርስቲያናችን ማስተማር የሚገባን ነገር ምንድነው?

5. ጸሎት።

ትምህርት ስምንት

ዘፍጥረት 20-23

የመጀመሪያ ቀን፡- ዘፍጥረት 20

አብርሃም ለብዙ ዓመታት ከእግዚአብሔር ጋር ተመላልሷል። በእነዚህም ዓመታት ውስጥ እምነቱ አድጓል። ባለፈው ሳምንት እግዚአብሔር ሰዶምን ለማጥፋት በነበረው እቅድ፥ ለአብርሃም ምሥጢሩን በማጫወት እንዴት እንዳከበረው ተመልክተናል። እንዲሁም እግዚአብሔር፥ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ልጅ እንደሚወለድ የተስፋ ቃል ገብቶለታል። ምንም እንኳ አብርሃም በብዙ የሕይወት ክፍሎቹ በሳል ቢሆንም፥ ለግል ደኅንነቱ ግን በእግዚአብሔር የመተማመን ችግር አልፎ አልፎ ይታይበት ነበር። ዛሬም አብርሃም

ከፍርሃት የተነሣ ሣራ እህቱ ብቻ እንጂ፥ ሚስቱ እንዳልሆነች በድጋሚ በመናገር እንዴት እንደዋሸ እንመለከታለን። አሁንም ከደካማነቱ የተነሣ፥ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎችና እቅዶች ከአደጋ ላይ ጣላቸው። ስለዚህ አብርሃምና ሣራን ለማዳንና ተስፋ ለተገባው ልጅ እቅዶቹን ከዳር ለማድረስ፥ እግዚአብሔር በጉዳዩ ውስጥ ጣልቃ መግባት ነበረበት። አንድ መሪ በእምነቱ ምንም ያህል የበሰለ ቢሆንም፥ እንዲሰናከል የሚያደርጉ የሕይወት ውጣ-ውረዶች ያጋጥሙታል። መሪው፥ እነዚህን ደካማ የሕይወቱን ክፍሎች ማወቅና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ድል መንሣት አለበት።

1ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) በአብርሃም ሕይወት ውስጥ ዳካማው ክፍል የትኛው ይመስልሃል?

ለ) በሕይወትህ ውስጥ ልትጠነቀቅባቸውና ለማሸነፍ መትጋት የሚኖርብህ የድካም ክልሎች የትኞቹ ናቸው?

2ኛ ጥያቄ፤ - ዘፍ. 20-23 አንብብ። በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የአብርሃምን የእምነት ጉዞ ግለጽ።

3ኛ ጥያቄ፤ ዘፍ. 20ን አንብብ።

ሀ) አብርሃም ወዴት ሄደ?

ለ) አብርሃምና ሣራ ያደረጉት ነገር ምን ነበር? ውጤቱስ?

ሐ) ይህ በዘፍጥረት 12፡10-20 ከተፈጸመው ነገር ጋር እንዴት ይመሳሰላል?

መ) እግዚአብሔር ለንጉሡ ምን ተናገረ?

ሠ) የንጉሡስ ምላሽ ምን ነበር?

ረ) አብርሃም በቁ. 7 ምን ተባለ? ለምን?

ሰ) አቢሜሌክ አብርሃምን ምን ብሎ ወቀሰው?

ሸ) አብርሃም ያቀረበው ምክንያት ምን ነበር?

ቀ) በአቢሜሌክ ቤተሰብ መፈወስ ውስጥ አብርሃም የተጫወተው ሚና ምን ነበር?

ለ) ከእዚህ ታሪክ ውስጥ የምንማረው አቢይ ትምህርት ምንድነው?

1. የአብርሃምና የሣራ እቅድ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች አደጋ ላይ ጣላቸው (ቁ. 1-2)።

ከሃያ አምስት ዓመታት በፊት አብርሃም ወደ ከነዓን ምድር መጥቷል። በዘፍ. 12፡10-20 ከዚያ በኋላ አብርሃም በከነዓን ምድር የነበረውን ረሃብ በመሸሽ እንዴት ወደ ግብፅ እንደ ወረደ ተመልክተናል። በዚያ ለሕይወቱ ከመስጋቱ የተነሣ፥ ሣራ እህቱ እንደሆነች በመናገር ዋሸ። የግብፅም ንጉሥ ሣራን ሚስት አድርጎ ወሰዳት። ከአብርሃም ፍርሃት የተነሣ፥ የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች በአደጋ ላይ ወድቀው ነበር። ዳሩ ግን እግዚአብሔር ጣልቃ ገባ። እግዚአብሔር በግብፃውያን ላይ ስለ ፈረደ፥ ሣራ ተለቀቀች። አሁንም ይኸው ታሪክ ሊደገም ነው - ለዚያውም በፍልስጤማውያን አገር ውስጥ።

አብርሃም ለጥቂት ጊዜ በመምሬ የአድባር ዛፍ አቅራቢያ ኖሯል (ዘፍ. 14፡13፤ 18፡1)። እግዚአብሔር ለአብርሃም ከተገለጸለትና በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ልጅ እንደሚሰጠው ተስፋ ከሰጠ በኋላ፥ አብርሃም ለመንቀሳቀስ ወሰነ። ለምን እንደተንቀሳቀሰ አናውቅም። ዳሩ ግን አብርሃም እንደ መንገደኛ በከነዓን ምድር በድንኳን ውስጥ እንደኖረ ልብ በል። በከነዓን ደቡብ ጫፍ አካባቢ ለመስፈር፥ በደቡብ አቅጣጫ ወደ አዜብ (ኔጌብ) ተጓዘ። ከዚያም ወደ ፍልስጤማውያን ምድር ዳር በመሄድ፥ በጌራራ ተቀመጠ (ከመጽሐፉ በስተጀርባ ያለውን ካርታ ተመልከት)። ይህም ለበርካታ ዓመታት የአብርሃም መኖሪያ ሆኖ ቆየ።

ሣራ ልጅ እንደምትወልድ የተሰጠው የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ሊፈጸም ተቃርቦ ነበር። ዳሩ ግን አሁንም ሰይጣን የእግዚአብሔርን እቅዶች ለማኮላሸት እየተጣጣረ ነበር። አብርሃም የታወቀበትን ሥፍራ ለቅቆ ወደ ሌላ አካባቢ ይሄድ ስለ ነበር፥ ፈራ። አብርሃምም፥ «ብዚህ ሥፍራ እግዚአብሔርን መፍራት በእውነት እንደሌለ፥ ለሚስቴም ሲሉ እንደሚገድሉኝ ስላሰብሁ ነው» በማለት ተናግሯል። ስለራሱ በመጨነቅ፥ አብርሃም አሁንም በእግዚአብሔር ላይ አለመተማመኑን

የሚያሳይ ተግባር አከናወነ። አብርሃም እግዚአብሔር ሕይወቱን በመቆጣጠር ላይ እንደነበረና ምንም ወይም ማንም ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ሊነካው እንደማይችል መረዳት ነበረበት። ዳሩ ግን ነገሮችን በራሱ እጅ በማከናወን፥ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች በአደጋ ላይ ጣላቸው።

ከፍርሃትና በእግዚአብሔር ላይ እምነት ከማጣት የተነሣ፥ አብርሃምና ሣራ ዋሹ። አብርሃም ለሁሉም ሰው ሣራ እህቱ እንደሆነች ተናገረ። በዕብራይስጡ «እህት» የሚለው ቃል፥ ብዙ ጊዜ ሚስቶች «እህቶች» ተብለው ከሚጠሩበት የአማርኛው ቃል ጋር ተመሳሳይ አሳብ የለውም። ለአይሁዶች እህት ማለት ሁለቱም ከአንድ አባት ወይም እናት የተወለዱ ናቸው ማለት ነው።

ምንም እንኳ ዘጠና ዓመት ቢሞላትም፥ ሣራ አሁንም ገና ውብ ነበረች። የጌራራ ንጉሥ አቢሜሌክ አያትና ለሚስትነት ወሰዳት። ከእርስዋ ጋር ከመተኛቱ በፊት ግን፥ እግዚአብሔር ያደረጋቸውን የተስፋ ቃሎችና እቅዶች ለመጠበቅ በጉዳዩ ውስጥ ጣልቃ ገባ። ምንም እንኳ አብርሃምና ሣራ ግማሽ እውነት ቢናገሩም፥ ዓላማቸው ለማታለል ነበር። ይህ ከአብርሃምና ከሣራ ልጅ ለማስገኘት እግዚአብሔር የወጠነውን እቅድ ማበላሸት ብቻ ሳይሆን፥ በንጹሐን ሰዎችም ላይ ፍርድ ሊያስከትልባቸው ነበር።

4ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) ብዙውን ጊዜ ክርስቲያኖች የሚፈሩባቸውንና በእግዚአብሔር ላይ እምነት የሚያጡባቸውን ሁኔታዎች ግለጽ።

ለ) እነዚህን ጊዜያት የሚፈሩት ለምንድነው?

ሐ) በዚያን ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ስለ ነበራቸው እምነት፥ ይህ ታሪክ ምን ያስተምራል?

2. እግዚአብሔር እቅዶቹን ለመጠበቅ ሲል ጣልቅ ይገባል (ቁ. 3-7)

አቢሜሌክ ሣራን ሚስት ለማድረግ እንደ ወሰደ፥ ወዲያውኑ እግዚአብሔር ራሱን ገለጠለት። ምንም እንኳን አቢሜሌክ ሣራ የአብርሃም ሚስት እንደ ነበረች ባለማወቁ ንጹሕ ቢሆንም፥ አሁንም

በእግዚአብሔር ፊት ጥፋተኛ ነበር። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁለት የኃጢአት ዓይነቶች አሉ። በመጀመሪያ፥ ኃጢአቱን የሚፈጽመው ሰው የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እየተላለፈ እንደሆነ እያወቀ የሚያደርገው ግልጽ ኃጢአት አለ። ደግሞም ሰውየው ምንም ስሕተት እንደሠራ ሳያውቅ የሚፈጸሙ ኃጢአቶች እንዳሉ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (ዘሌ. 5፡17 ተመልከት)። እነዚህም ቢሆኑ በቅዱሱ አምላክ ፊት ስሕተቶች ነበሩ።

ከዝሙት የተነሣ እግዚአብሔር አቢሜሌክን እንዴት በከፋ ሁኔታ ሊፈርድበት እንደነበር ልብ በል። እግዚአብሔር እንደሚሞት ነገረው። ዝሙት ቤትን ስለሚያፈርስ፥ የእግዚአብሔርም ቃል አድራጎቱ ምን ያህል የከፋ እንደሆነ ሁል ጊዜም ያሳያል። ዝሙት ለሴትም ሆነ ለወንድ እኩል የተወገዘ ነው። በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት ትልቅ ክፋት ነው።

5ኛ ጥያቄ፤ ሀ) ብዙ ሰዎች፥ ዝሙት፥ በተለይም ለወንዱ እጅግም የከፋ ስሕተት እንዳልሆነ የሚያስቡት ለምንድነው?

ለ) ዝሙት ስሕተት የሚሆነው ለምንድነው?

ሐ) በዝሙት ላይ ጠንካራ ቃል የሚናገሩ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የትኞቹ ናቸው?

በብዙ መንገዶች አቢሜሌክ ከአብርሃም የበለጠ ፈርሃ-እግዚአብሔርን አሳይቷል። አብርሃም በምዕራፍ 18 ውስጥ እንዳደረገው፥ አቢሜሌክ በእግዚአብሔር ይቅር ባይ ባሕርይ ላይ በመተማመን፥ ስለን ንጽሕናው ተከራክሯል። እግዚአብሔር ንጹሑን ሕዝብ እንደማያጠፋ አቢሜሌክ ያውቅ ነበር። እርሱና ሕዝቡ በጥፋት ጫፍ ላይ የደረሱት፥ በግራ ጦስና አብርሃም በተናገረው ነገር እንደሆነ ግልጽ ሆኖለት ነበር።

አቢሜሌክ እያወቀ ዝሙት ከመፈጸም ንጹሕ እንደሆነ እግዚአብሔርም ተስማምቷል። እንዲሁም እግዚአብሔር አቤሜሌክን ከግራ ጋር እንዳይተኛ በማገድ፥ ከከፋ ኃጢአት እንደጠበቀው «እኔም ደግሞ በፊቴ ኃጢአትን እንዳትሠራ ከለከልሁህ» ብሎ ተናግሯል። ስለሆነም እግዚአብሔር ለአቢሜሌክ በቤቱ ላይ የወረደውን እርግማን እንዴት እንደሚያስወግድ ነገረው።

እግዚአብሔር ለአቢሜሌክ ሁለት ነገሮችን እንዲያደርግ ነገረው፡- በመጀመሪያ፥ ሣራን ወዲያውኑ ለአብርሃም መመለስ ነበረበት። ሁለተኛ፥ ከእግዚአብሔር ፍርድ ነጻ ለመውጣት ወደ አብርሃም መሄድ ነበረበት። እግዚአብሔር አቢሜሌክን ወደ አብርሃም እንዲሄድ መናገሩ አስደናቂ ነገር ነው። በመጀመሪያ ችግሩን የቆሰቆሰው የአብርሃም የእምነት ማጣት ነበር። ዳሩ ግን እግዚአብሔር አብርሃምን እንደ «ነቢዩ» እና «ካህኑ» አድርጎ ይገልጸዋል።

6ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) ነቢይ ምን ማለት ነው?

ለ) አብርሃም ነቢይ የሆነው በምን መንገድ ነበር?

ሐ) አብርሃም እንደ ካህን ሆኖ የሠራው በምን መንገድ ነበር?

ነቢይ የእግዚአብሔር ቃል አቀባይ የሆነ ሰው ነው። የእግዚአብሔርን መልእክት በቀጥታ ከእግዚአብሔር በማግኘት፥ ያንኑ መልእክት ወደ ሕዝቡ ያስተጋባል። ከነቢይ መልእክቶች መካከል አንዱ ወደፊት ስለሚፈጸመው ነገር መተንበይ ነበር። ዳሩ ግን ብዙውን ጊዜ የነቢይ መልእክት የሚያተኩረው በመጪው ጊዜ ላይ ሳይሆን፥ በዚያኑ ወቅት ሕዝቡ እንዲሰማ እግዚአብሔር በፈለገው መልእክት ላይ ነበር። ምንም እንኳ ስለ ብሉይ ኪዳን ነቢያት ሲወሳ፥ ስለ ወደፊት እንደተናገሩ ሰዎች አድርገን ብናስብም፥ ከነቢያቱ መካከል አንዳንዶቹ ስለ ወደፊቱ በጭራሽ አልተናገሩም (ለምሳሌ ዮናስ)። የእግዚአብሔርን መልእክት ለሕዝቡ አስተላልፈዋል። እግዚአብሔር ስለ ተናገረውና ለሰዎች የሚሆን መልእክት ስለ ሰጠው፥ አብርሃም ነቢይ ነበረ። አብርሃም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነቢይ ተብሎ በመጠራት የመጀመሪያው ሰው ነበር። እንዲሁም አብርሃም በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል መካከለኛ እንደሚሆን ካህንም ነበር። እግዚአብሔር ለአቢሜሌክ እንዲጸልይና እንዲግልድ ኃላፊነት ሰጠው።

በዚህ ታሪክ ውስጥ፥ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን አሕዛብን በመባረክ ሊኖራቸው የሚገባውን አስፈላጊ ሚና እያሳየ ነበር። እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለትውልዶቹ ከሰጣቸው የተስፋ ቃሎች መካከል አንዱ ለአሕዛብ ሁሉ በረከት እንደሚሆኑ እንደ ነበረ ታስታውሳለህ። እስራኤላውያን ከዓለም ጋር ባላቸው ግንኙነት

በሚከተሉት ሁለት መንገዶች ማገልገል ነበረባቸው። በመጀመሪያ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን፥ ለዓለሙ ሁሉ የሚያውጁ ነቢያት መሆን ነበረባቸው። ባመዛኙ በአይሁዶች የተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ የዚህ ሚና ፍጻሜ ውጤት ነው። ሁለተኛ፥ አይሁዶች አሕዛብን በእግዚአብሔር ፊት የሚያቀርቡ መካከለኞች፥ ካህናት መሆን ነበረባቸው (ዘጸ. 19:5 ተመልከት)።

7ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) ዛሬ እኛ ከዓለም ጋር ያለን ግንኙነት፥ አብርሃም ከአቢሜሌክ ጋር ከነበረው ግንኙነት የሚመሳሰለው እንዴት ነው? (1ኛ ጴጥ. 2:9 ተመልከት)።

ለ) አንተና ቤተ ክርስቲያንህ ይህንን እየፈጸማችሁ ያላችሁባቸውን መንገዶች ግለጽ።

8ኛ ጥያቄ፤ - ኃጢአት በሚሠሩበት ጊዜ እንኳ፥ እግዚአብሔር በልጆቹ በኩል እንደሚሠራ ከእነዚህ ጥቅሶች ምን እንማራለን?

3. አቢሜሌክ እግዚአብሔርን ታዘዘ (ቁ. 8-18)

ጎሕ እንደቀደደ፥ አቢሜሌክ በእግዚአብሔር ላይ የነበረውን እምነት በሙሉ መታዘዝ አሳየ። በመጀመሪያ የሕዝቡን መሪዎች ጠራቸውና እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ስላመጣው መርገም ነገራቸው። ይህም በሕዝቡ መካከል ታላቅ የፍርሃት ስሜት ቈረ። በዚህ ጊዜ አሕዛቦቹ ከአብርሃም የበለጠ ፈርሃ-እግዚአብሔር ይታይባቸው ነበር። አቢሜሌክ አብርሃም ወደ ነበረበት ሥፍራ ለመድረስ ፈጠነ። በዚያም አብርሃምን ስለ ኃጢአቱ ወቀሰው።

9ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) ብዙ ክርስቲያኖች ለሕይወታቸው በእግዚአብሔር የመተማመን ተመሳሳይ ችግር ያለባቸው እንዴት ነው?

ለ) ብዙ ክርስቲያኖች ራሳቸውን ለመጠበቅ ወይም የሚፈልጉትን ነገር ለማግኘት የሚዋሹት ለምንድነው?

ሐ) በቤተ ክርስቲያንህ መዋሸትን በመንቀፍ ለማስተማር በዚህ ታሪክ እንዴት ለመጠቀም ትችላለህ?

ምንም እንኳ ጥፋቱን አምኖ መቀበል ቢገባውም፥ አብርሃም ማመካኛዎችን ማቅረብ ጀመረ። በመጀመሪያ፥ ፍልስጤኤማውያንን

ወቀሰ። እግዚአብሔርን እንደማይፈሩ ስለተሰማው፥ ለመዋሸት እንደተገደደ ተናገረ። ይሁን እንጂ አቢሜሌክና ሕዝቡ ከአብርሃም የበለጠ ፈርሃ-እግዚአብሔር አሳይተዋል። እንዲሁም ሣራ ግማሽ እህቱ ስለ ነበረች፥ ግማሽ ውሸት ብቻ እንደ ተናገረ ገልጿል።

አብርሃምና ሣራ ይህን ታሪክ ከዚህ በፊት ብዙ ጊዜ እንደተጠቀሙበት ግልጽ ነው። ገና በዘፍጥረት 12 እንደ «ተቅበዝባዥ» ሆነው ለመኖር ካራንን በለቀቁ ጊዜ ነበር የጀመሩት። አብርሃም በሆነ ምክንያት እግዚአብሔር ሕይወቱን እንደሚጠብቅ አላመነም ነበር። ይልቁንም ራሱን በውሸት ካባ ለመደበቅ ሞከረ።

በዚህ ታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር የአብርሃምን ሥራዎች እያጸደቀለት አልነበረም። ይልቁንም ታሪኩ ራሳችንን ለመጠበቅ ወይም የኑሮ ሁኔታችንን ለማሻሻል ብለን መዋሸት እንደሌለብን ያስተምረናል። አብርሃምና ሣራ በእግዚአብሔር ቢተማመኑና እውነትን ቢናገሩ ኖሮ፥ እንዲህ ባለ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ አይገቡም ነበር።

አቢሜሌክ የነበጠውን ነገር ለማቅናትና የአብርሃምንና የእግዚአብሔርን ሞገስ ለማግኘት ብዙ ጥረት አድርጓል። በመጀመሪያ፥ አቢሜሌክ ለአብርሃም ከብቶችና ባሪያዎች የመሳሰሉ በርካታ ንብረቶችን ሰጠው። በግብፅ እንደታየው ሁሉ፥ ምንም እንኳን አብርሃም በፈጸመው ስሕተት ጥፋተኛ ቢሆንም፥ የንብረት በረከት አግኝቷል። ሁለተኛ፥ አቤሜሌክ እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር እንደነበረና እንደሚባርከው በማመን፥ ምድሪቱን አብርሃም እንዲኖርባት ፈቀደለት። ሦስተኛ፥ አቢሜሌክ ለሣራ የሺህ (ሰቅል) ሚዛን ብር ሰጣት። ይህም 12 ኪሎ ግራም የሚመዝን ብር ሲሆን፥ የደረሰባትን የስሜት ውድቀት ወይም የተሰማትን ኃፍረት ለማካካስ ነበር።

10ኛ ጥያቄ I- በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ-ቃላት ውስጥ «ሰቅል» የሚለውን ቃል ተመልከት።

ከዚያም ካህኑ አብርሃም ወደ እግዚአብሔር ጸለየ። ከጸሎቱም የተነሣ፥ እግዚአብሔር ልጆችን መውለድ እንዲችሉ፥ በአቢሜሌክ ቤት ያሉትን ሴቶች ሁሉ ማህፀኖች ከፈተ። ምንም እንኳ እግዚአብሔር ለአብርሃም የምልጃን ጸሎት ሚና ቢሰጠውም፥ ማህፀንን የመዝጋትና

የመከፈት፥ ሕይወትን የማኖርና የመውሰድ ሥልጣን የነበረው እግዚአብሔር እንጂ፥ አብርሃም እንዳልነበረ ግልጽ ነው። እግዚአብሔር በምድር ላይ ከኖሩት ነገሥታት ሁሉ በላይ ነው።

አብርሃምና እስራኤል ለሕዝቦች ነቢያትና ካህናት መሆን ነበረባቸው። ሆኖም ይህን ለማድረጋቸው፥ በሕዝቦች መካከል መልካም ምስክርነት ቢኖራቸው ኖሮ፥ ምንኛ ባማረ ነበር! አብርሃምና የእስራኤል ሕዝቦች በእግዚአብሔር ፊት በንጽሕና ባለመኖርና በእምነት ባለመመላለስ በደለኞች ነበሩ። በአቅራቢያቸው ለሚኖሩ አሕዛቦችም የሚሰጡት ምስክርነት ደካማ ነበር።

11ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) ይህ ቤተ ክርስቲያን ከዓለም ጋር ካላት ግንኙነት የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

ለ) ቤተ ክርስቲያንም ለሕዝቦች እንደ ነቢይ ወይም እንደ ካህን የምትሆንባቸውን ሁኔታዎች ግለጽ (1ኛ ጴጥ. 2፡9 ተመልከት)።

ሐ) የአብርሃም ሕይወት ሁል ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ከሚፈጸመው ሁኔታ ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

እኛ የዓለም ብርሃን መሆን አለብን። ዳሩ ግን ብዙውን ጊዜ ባለመታዘዝ በተበላሸ ምስክርነት የእግዚአብሔርን እቅዶች በአደጋ ላይ እንጥላለን። ይህ በግለሰብ ደረጃና በቤተ ክርስቲያን ደረጃ ወደ ንስሐና እግዚአብሔርን በመታዘዝ፥ ንጹሕ ኑሮ ለመኖር ወደ መሻት ሊመራን ይገባል። ይሁን እንጂ፥ በዚህ ሁሉ የሚያጽናናን እግዚአብሔር በስሕተቶቻችን እንደማይወሰን በማወቅ የሚሰማን ድፍረት ነው። ኃጢአተኞችንና ስሕተቶችን በማስወገድ፥ ዓላማዎቹን ይፈጽማል። አምላካችን ሁሉን ቻይ ነው!

12ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) ብዙውን ጊዜ ለመታዘዝ የሚሳኑን፥ እግዚአብሔር እንድንታዘዛቸው የሰጠን ትዕዛዛት ምንድናቸው?

ለ) ለዚህ ጉዳይ በግልና በቤተ ክርስቲያን ደረጃ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ለመጠየቅ ጊዜ ውሰዱ።

ሐ) እግዚአብሔር ከኃጢአቶቻችንና ከድካሞቻችን ሁሉ በላይ በመሆኑና ሁኔታዎችንም በመቆጣጠሩ፥ በምን መንገድ ልንጽናና እንችላለን?

ሁለተኛ ቀን ፡- ዘፍጥረት 21

ዘፍጥረት 21 ሦስት ታሪኮችን ይዟል። በመጀመሪያ፥ ስለ ይስሐቅ መወለድ እንሰማለን። ሁለተኛ፥ ስለ እስማኤልና አጋር መባረር እናነባለን። እንዲሁም ሦስተኛ፥ በአብርሃምና በአቢሜሌክ መካከል ስለተደረገው ቃል ኪዳን እናነባለን። ከእነዚህ ሦስት ታሪኮች ውስጥ እያንዳንዱ ታሪክ የተለያየ ትምህርት ያስተላለፋል።

13ኛ ጥያቄ፤ - ዘፍጥረት 21ን አንብብ። ሀ) ይስሐቅ በተወለደ ጊዜ አብርሃምና ሣራ ስንት ዓመታቸው ነበር?

ለ) ከቁ. 1-7 ይስሐቅ ወይም «ሣቅ» የሚሉት ስሞች ስንት ጊዜ ተጠቅሰዋል።

ሐ) አብርሃም እግዚአብሔር ለሰጠው የቀድሞ ትዕዛዝ መታዘዙን እንዴት አሳየ?

መ) በሣራና በእስማኤል መካከል የተነሣው ችግር ምን ነበር?

ሠ) አብርሃም ምን እንዲያደርግ ጠየቀችው?

ረ) እግዚአብሔር አብርሃም ምን እንዲያደርግ ነገረው?

ሰ) እግዚአብሔር እስማኤልን በተመለከተ፥ ለአብርሃም ምን የተስፋ ቃል ሰጠው?

ሸ) ለአጋር የተገለጸላት ማን ነበር?

ቀ) እግዚአብሔር የአብርሃም ልጅ በሆነው እስማኤል ላይ ምህረቱን እንዴት አሳየ?

በ) እግዚአብሔር ለአጋር የሰጠው የተስፋ ቃል ምን ነበር?

ረ) በአብርሃምና በአቢሜሌክ መካከል የተፈጠረው ችግር ምን ነበር?

ቸ) አብርሃም ከእግዚአብሔር ጋር ስለነበረው ግንኙነት አቢሜሌክ ምን ያውቅ ነበር?

ኃ) ሁለቱስ ምን ቃል ኪዳን አደረጉ?

ነ) አብርሃም ለእግዚአብሔር የሰጠው ስም ምን የሚል ነበር?

ኘ) ከሦስቱ ታሪኮች ከእያንዳንዳቸው የምንማራቸውን ሦስት አበይት ትምህርቶች ዘርዝር።

1. የይስሐቅ መወለድ (21፡1-7)

ከሃያ አምስት ዓመታት በፊት፥ እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለሣራ የቤተሰብ ሐረጋቸውን የሚቀጥል ልጅ እንደሚሰጥ ተስፋ ሰጥቶአቸው ነበር። ለሃያ አምስት ዓመታት ጠበቁ። ከዚያም በራሳቸው ኃይል ልጅ ለማግኘት ቢሞክሩም፥ እግዚአብሔር እስማኤልን ከአብርሃም ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ወራሽ እንዳይሆን ከልክሎአል። በመጨረሻም የተስፋውን ልጅ የሚያገኙበት ጊዜ ደረሰ። ልጅ የተሰጣቸው፥ እምነት ስለነበራቸው ወይም ለእግዚአብሔር አንድ ትልቅ ሥራ ስለሠሩ ሳይሆን፥ ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ ብቻ ነበር። የዘጠና ዓመቷ ሣራ ለመቶ ዓመቱ አብርሃም ልጅ የወለደችለት ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ ነበር። ይስሐቅ የተወለደው በ2066 ዓ.ዓ. አካባቢ ነበር።

ሙሴ ስለ ይስሐቅ ልደት በመተረክ ብዙ ጊዜ አለመውሰዱ አስገራሚ ነው። ስለ ይስሐቅ ልደት የተሰጠውን የተስፋ ቃል በመተረክ 9 ምዕራፎች ሲወሰድ፥ አሁን ግን የይስሐቅን መወለድ በ 7 ቁጥሮች ብቻ ይነግረናል።

ሙሴ ለእስራኤላውያንና ለእኛ ሊያስታውሰን የሚፈልጋቸው ሦስት አበይት ነገሮች ነበሩት፡- በመጀመሪያ፥ ሙሴ እግዚአብሔር ሁል ጊዜም የተስፋ ቃሎቹን የሚጠብቅ አምላክ እንደሆነ ለማሳየት ይፈልጋል። እግዚአብሔር የሰጠንን የተስፋ ቃል እኛ እንደምንፈልገው በፍጥነት ባይፈጽምልንም፥ የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች ከፍጻሜ እንደሚደርሱ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ሊተማመኑ ይችላሉ። ሙሴ በተደጋጋሚ እግዚአብሔር «እንደተናገረው» አደረገ፤ «ተስፋ

እንደሰጠው» አሰበ ይላል (በሁለት ቁጥሮች ውስጥ ሦስት ጊዜ ተደጋግሟል)።

14ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) ለክርስቲያኖች ከተሰጡት የተስፋ ቃሎች መካከል ገና ሙሉ ለሙሉ ያልተፈጸሙትን አንዳንዶቹን ዘርዝር።

ለ) ለክርስቲያኖች እግዚአብሔር ሁል ጊዜም የተስፋ ቃሎቹን የሚፈጽም አምላክ መሆኑን ማወቅ ለምን ይረባል?

ሁለተኛ፥ ሙሴ አብርሃም ለእግዚአብሔር ቃል እንደታዘዘ አመልክቷል። አብርሃም ልጁን እንደ ታዘዘው «ይስሐቅ» ብሎ ሰይሞታል። እንዲሁም እግዚአብሔር እንዳዘዘው በስምንተኛው ቀን ገርዞታል። በዚህ የበረከት ጊዜ፥ አብርሃም እግዚአብሔርን በጥንቃቄ ይታዘዝ ነበር።

ሦስተኛ፥ ሙሴ የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች ከመፈጸማቸው የተነሣ በቤተሰቡ ውስጥ የነበረውን ታላቅ ደስታ ያሳያል። ሙሴ ይህንን ደስታ በልጁ በይስሐቅ ስም አወጣጥ ላይ የነበረውን የቃላት ጨዋታ በመጠቀም ያሳያል። ይስሐቅ ማለት «ሣቀ» ማለት መሆኑን ታስታውሳለህ። ከአንድ ዓመት በፊት አብርሃም (ዘፍ. 17፡17) እና ሣራ (ዘፍ. 18፡12) ሁለቱም በጥርጣሬ ስቀው ነበር። አሁን ያ የጥርጣሬ ሳቃቸው ወደ ደስታ ሳቅ ተለውጧል። ተአምር ተፈጠረ። ሽማግሌው አብርሃም ከአርጊቷ ሣራ ወንድ ልጅ ወለደ። በዚያ ቤት ውስጥ ምን ያህል ደስታ ሆኖ ይሆን? ከዓመታት መጠባበቅ በኋላ፥ የተስፋው ልጅ ተወለደ። የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች ተፈጸሙ። እንደወትሮው፥ እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን በራሱ መንገድ ሲፈጽም፥ የእግዚአብሔር ልጆች በደስታ ሙላት ይፍለቀለቃሉ።

15ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) በዮሐ. 15፡11 ኢየሱስ የሰጠን የተስፋ ቃል ምንድነው?

ለ) ይህ ደስታ በሕይወትህ ውስጥ የሚታየው እንዴት ነው?

2. አጋርና እስማኤል ተባረሩ (21፡8-20)

ብዙም ሳይቆይ ይህ ደስታ ወደ ቁጣና ቅንዓት ተለወጠ። በአጋርና ሣራ መካከል የነበረው መራርነት እንደገና አገረሸ። አብርሃምና ሣራ

እንደ ሥጋ ፈቃድ የተመላለሱበት ጊዜ ትዝታ ደግሞ ያስጨንቃቸው ጀመር።

ችግሩም የተቆሰቆሰው ሣራ ለይስሐቅ ታላቅ ግብዣ ባዘጋጀች ጊዜ ነበር። በጥንት ጊዜ ሰዎች ልጆችን ከእናቶቻቸው ጡት የሚያስጥሉበት ወቅት በዚህ የዕድሜ ክልል በመሆኑ፥ ይስሐቅ ምናልባት ሦስት ወይም ሁለት ዓመት ሳይሆነው አይቀርም። በአንዳንድ የኢትዮጵያ ክፍሎች እንደሚደረገው ሁሉ የማውጣት ሥነ-ሥርዓት፥ ወላጆች ልጁ በሕይወት እንደሚሰነብት እርግጠኞች የሚሆኑበትና ከሕፃንነት ወደ ልጅነት የሚሸጋገርበት በመሆኑ፥ ይህ የደስታ ጊዜ ነበር። በግብዣው ወቅት፥ ሣራን ያስቆጣት አንድ ነገር በእስማኤልና በይስሐቅ መካከል ተፈጸመ። እስማኤል ምን እንዳደረገ አናውቅም። «መሳለቅ» የሚለው ቃል በዕብራይስጥ ሁለት ትርጉሞች ሊኖሩት ይችላል። በመጀመሪያ፥ «መጫወት» ሊሆን ይችላል። በታሪኩ ውስጥ የተገለጸው መሳለቅ (መሳቅ) ይህንን ለማለት ከሆነ፥ ችግሩ የተነሣው ሣራ የባሪያዪቱ ልጅ የሆነው እስማኤል፥ የቃል ኪዳኑ ወራሽ ከሆነው ከይስሐቅ ጋር እንደ እኩል ሆኖ ሲጫወት ስላየች ነው። አለበለዚያ ግን መሳለቅ ማለት ልጁን መሳለቂያና መቀለጃ ማድረግ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ፥ ዋናው ችግር ሣራ የአብርሃም ታላቅ ልጅ የሆነው እስማኤል፥ በይስሐቅ ወራሽነት ላይ ችግር እንዳይፈጥር መፍራቷ ነበር። በቁጣና በቅንዓት፥ አብርሃም አጋርንንና እስማኤልን ከቤት እንዲያባርራቸው ጠየቀች። ሣራ ቤትና ሥራ ለሌላት አጋርና የአብርሃም ልጅ ለሆነው እስማኤል ግድ አልነበራትም። የት ይደርሳሉ? ብላም አላሰበችም።

ይህ በሁለት ሴቶች መካከል ይካሄድ የነበረው ሽኩቻ ለአብርሃም የራስ ምታት ሆነበት። አብርሃም ከአሥራ ሰባት ዓመታት በላይ ብቸኛ ልጁ አድርጎ ሲንከባከበው የቆየውን እስማኤልን መውደዱ መቼም አይጠረጠርም። አብርሃም ከቤት ሊያባርራቸው አልፈለገም ነበር። በጊዜውም እንደነበረው ልማዳዊ ሕግ፥ አብርሃም የባሪያውን ልጅ እንዲያባርር አይፈቅድለትም ነበር። ይሁንና እግዚአብሔር አጋርና እስማኤልን እንዲያባርራቸው ነገረው።

16ኛ ጥያቄ፤ - እግዚአብሔር አብርሃምን አጋርና እስማኤልን እንዲያባርር የተናገረው ለምን ይመስልሃል?

ምንም እንኳ ይህ በጣም ጭካኔ የተሞላበት ድርጊት ቢመስልም፥ እግዚአብሔር የይስሐቅን ውርስና እቅዶቹን ለመጠበቅ የተጠቀመበት መንገድ ነው። እንደምንመለከተው፥ እግዚአብሔር አጋርን ወይም እስማኤልን አልተዋቸውም። የእስማኤልን የወደፊት ሕይወት በተመለከተ፥ እግዚአብሔር ለአብርሃም የተስፋ ቃል ሰጥቶታል። የአብርሃም ልጅ እንደመሆኑ፥ የተባረከና ታላቅ ሕዝብ የሚሆን ነበር። እስማኤል በዚህ ጊዜ ትንሽ ልጅ እንዳልሆነ ልብ በል። ቢያንስ 17 ዓመት ይሆነዋል።

እየተጨነቀና ዳሩ ግን እግዚአብሔር እንደሚጠነቀቅላቸው እየተማመነ፥ አብርሃም ለአጋርና እስማኤል ትንሽ ምግብ ሰጥቶ በጠዋቱ ሸኛቸው። አጋርና እስማኤል የደቡብን አቅጣጫ ይዘው ተጓዙ። ምናልባትም ወደ አጋር አገር የሚወስደውን የግብፅ መንገድ ይዘው ይሆናል። ወዲያውኑ ምግባቸውና ውኃቸው አለቀባቸው። አጋር የሚሞቱ ስለመሰላትና ልጁ እስማኤል ሲሞት ላለማየት ስለፈለገች፥ ልጁን ከቁጥቋጦው ሥር አስቀምጣ፥ ትንሽ ርቀት ፈቀቅ አለች። እርስዋና ልጁ ሁለቱም ተስፋ በመቁረጥ ማልቀስ ጀመሩ።

ለሁለተኛ ጊዜ እግዚአብሔር፥ በ «እግዚአብሔር መልአክ» አምሳል ሆኖ፥ ከአጋር ጋር ሊነጋገር መጣ። እስማኤል የሚለውን ስም ትርጉም አስታውስ። በዕብራይስጥ «እግዚአብሔር ይሰማል» ማለት ነው። እግዚአብሔር የእስማኤልን ድምፅ ሰማ። አሁንም እግዚአብሔር ስለ ልጁ የወደፊት ሕይወት ለአጋር የተስፋ ቃል ሰጣት። እስማኤል ታላቅ ሕዝብ የሚሆን እንጂ፥ በምድረ በዳ የሚሞት ሰው አልነበረም። አጋር በአብርሃምና ሣራ በደረሱባት ችግሮች ስለተተበተበች ምንም ምርጫ አልነበራትም። ዳሩ ግን ለተጣሉትና ላልታደሉት ልዩ ፍቅር የሚያሳየው አምላክ፥ በምድረ በዳ በፍቅሩ ተገለጸና አጽናናት። በዚያ በበረሃ እግዚአብሔር ለአጋርና ለእስማኤል ውኃ ሰጣቸው።

እግዚአብሔር አጋርንና እስማኤልን አዳናቸው። ምንም እንኳ በምድራዊ አባቱ የተባረረ ቢሆንም፥ እግዚአብሔር ለእስማኤል ተጠነቀቀለት። በምድረ በዳ መኖር ጀመሩና እስማኤል ተቅበዝባዥና ተዋጊ (ቀስተኛ) ሆነ። ካደገ በኋላ፥ ከእናቱ አገር ከግብፅ ሚስት አገባ።

ይህ የአጋርና የእስማኤል ታሪክ፥ በብዙ መንገዶች በእስራኤል ሕዝብ ላይ የሚሆነው ነገር ተምሳሌት ነው። በሙሴ መሪነት እነርሱም በምድረ በዳ ለመቅበዝበዝ ተገድደው ነበር። እግዚአብሔርም ለነ እስማኤል እንዳደረገው፥ ውኃ አጠጥቶአቸዋል።

ጳውሎስ በገላትያ መጽሐፉ ውስጥ ይህንን ታሪክ፥ በማያምኑና በሚያምኑ፥ በሕግ ተከታዮችና በኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች መካከል ላለው ግንኙነት ተምሳሌት አድርጎ አቅርቦታል (ገላ. 4፡21-31)። ያለ እግዚአብሔር መለኮታዊ አሠራር፥ በተፈጥሮአዊ ሁኔታ የተወለደው እስማኤል፥ በእስር ውስጥ ያለው የማያምን ሰው ምሳሌ ነው። በተለይም በሕግ እስራት ውስጥ ያሉት አይሁዶች ምሳሌ ነው። ለአብርሃም በተአምር የተወለደው ይስሐቅ፥ በመንፈስ እንጂ በተፈጥሮአዊ ሁኔታ የማይመላለሱ የእግዚአብሔር መንፈሳዊ ልጆች የሆኑት አማኞች ምልክት ነው። በእስማኤልና በይስሐቅ መካከል የሚታየው ጦርነት፥ ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔር ልጆች ባልሆኑት ሰዎች አማካይነት በአማኞች ላይ የሚፈጸም ስደት ምልክት ነው።

ይህ የአጋርና የእስማኤል ታሪክ በጣም አሳዛኝ ነው። ይሁንና አስፈላጊ እውነቶችን ያስተምረናል። በመጀመሪያ በሥጋ የመመላለስን አሳዛኝ ውጤቶች ያስተምረናል። ሁለተኛ፥ ለእግዚአብሔር እቅዶች መፈጸም እንቅፋት በመሆኑ፥ እግዚአብሔር አብርሃምን እስማኤልን ከቤቱ እንዲያስወጣ እንደተናገረው፥ እንደዚሁም በሕይወታችን ውስጥ የእርሱ ፈቃድ አንዳይፈጸም እንቅፋት የሚሆኑትን ነገሮች ሁሉ እንድናስወግድ ይፈልግብናል። ብዙውን ጊዜ እነዚህ ነገሮች የምንወዳቸው ናቸው። አብርሃም እስማኤልን ይወደው ነበር። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ፈቃድ ይፈጸም ዘንድ እስማኤል መሄድ ነበረበት። ምንም እንኳ መልካም ቢሆኑም፥ በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንድናድግ ከተፈለገ ከሕይወታችን ውስጥ መወገድ የሚገባቸው በርካታ ነገሮች አሉ። ሙሉ ለሙሉ ራሳችንን ሰጥተን እግዚአብሔርን እንዳንከተል የሚከለክለን ነገር ሁሉ፥ ጠላታችን ነው።

17ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) መልካም ቢሆኑም ቅሉ፥ የክርስቲያንን ዕድገት ሊያቀጭጩ የሚችሉትን አንዳንድ ነገሮች ዘርዝር። ሕይወትህን መርምር።

ለ) በሕይወትህ ውስጥ ዕድገትህን የሚገቱ ነገሮች ካሉ፥ ለእግዚአብሔር ተናዘዝና እነዚህን ነገሮችን አስወግድ።

3. በቤርሳቤህ የተደረገ ቃል ኪዳን (21፡22-34)

ዘፍጥረት 21፡22-34 ትረካውን የሚቀጥለው አብርሃም በፍልስጤኤም ምድር ከነበረበት ከዘፍጥረት (8፡10) በመነሣት ነው። አብርሃም ከፍልስጤኤማውያን ጋር መኖሩን ተያያዘው። ንጉሥ አቢሜሌክ ስለ እርሱ ሁለት ነገሮች ተረድቶ ነበር፡- በመጀመሪያ፥ አሕዛብ ሕይወቱን ሲያጤኑ፥ እግዚአብሔር በተለየ መንገድ ከእርሱ ጋር እንደ ነበረ ተረድተዋል። አብርሃም ከእግዚአብሔር ጋር የተለየ ግንኙነት እንደ ነበረው በመረዳት፥ እነርሱም ከዚያ በረከት ተቋዳሽ ለመሆን ፈለጉ። ሁለተኛ፥ አብርሃም ሙሉ ለሙሉ የሚታመኑበት ሰው አለመሆኑንና አደጋ እንደሚያደርሱበት ከተሰማው እንደሚዋሽ ያውቁ ነበር። ከእነዚህ ሁለት እውነታዎች የተነሣ አቢሜሌክና የሠራዊቱ አዛዥ ፊኮል ከአብርሃም ጋር የሰላም ቃል ኪዳን ለማድረግ ወሰኑ።

በጋራ ቸርነት የማድረጉን ቃል ኪዳን እንደሚያከብር መጀመሪያ አብርሃም በቃል ተስማማ። ዳሩ ግን የአቢሜሌክ ባሪያዎች ቃል ኪዳኑን በመጋፋት የውኃ ጉድጓድ ስለነጠቁት፥ ወዲያውኑ በአብርሃምና በአቢሜሌክ መካከል ችግሮች መፈጠር ጀመሩ። ጠቡም በውኃ ጉድጓዱ ባለቤትነት ላይ የተመሠረተ ነበር። አብርሃም በአቢሜሌክ ላይ ወቀሳ ሰነዘረ። አቢሜሌክ ግን ባሪያዎቹ የውኃ ጉድጓዱን እንደነጠቁት እንደማያውቅ ገለጠ። አብርሃም ቃል ኪዳኑን ከአቢሜሌክ ጋር ለማተም፥ በጎችና ከብቶች በማምጣት ለአቢሜሌክ ሰጠው። እነዚህ በጎችና ከብቶች ቃል ኪዳኑን የማተሙ ሥነ-ሥርዓት ክፍሎች ይሆናሉ። ቃል ኪዳኑም የተደረገበት ሥፍራ ቤርሳቤህ ተባለ።

ቤርሳቤህ ሁለት ፍቺዎች ሊኖሩት ይችላል፡- በመጀመሪያ፥ «የሰባት የውኃ ጉድጓድ» ማለት ሊሆን ይችላል። ይህም የውኃው ጉድጓድ በአብርሃም መቆፈሩን ለማረጋገጥ በዚያ ከቆሙት ሰባት በጎች የተነሣ ነው። ሁለተኛ፥ «የመሀላ ጉድጓድ» ሊባል ይችላል። ምክንያቱም አብርሃምና አቢሜሌክ ቃል ኪዳናቸውን በመሀላ ያጸኑት በዚህ ሥፍራ ስለ ነበር ነው (ስለ ጉድጓዱ በድጋሚ መሰየም ዘፍ.

26፡32-33 ተመልከት)። ከብዙ ዓመታት በኋላ ቤርሳቤህ የእስራኤል ምድር ደቡባዊ ዳርቻ ሆናለች (2ኛ ሳሙ. 17፡11)።

በዚያ በቤርሳቤህ አብርሃም የተምር ዛፍ ተከለ። ይህ ዛፍ በርካታ ዓላማዎች ነበሩት። ዛፉ አብርሃም በዚያ አካባቢ ለመኖር መወሰኑን ያመለክታል። ዛፎች የእግዚአብሔር ስጦታ ምልክቶች ከመሆናቸውም በላይ፥ ከመገናኛ ድንኳን ዘመን በፊት፥ የተወሰኑ ዛፎች ብዙ ጊዜ የማምለኪያ ሥፍራዎች በመሆን አገልግለዋል። ዛሬ አንዳንድ ሰዎች እንደሚያደርጉት፥ አብርሃም ዛፍን አያመልክም ነበር። ይልቁንም ዛፉን የማምለኪያ ሥፍራ አድርጎ ይጠቀምበት ነበር።

በመጨረሻ፥ በዚያው በቤርሳቤህ አብርሃም «የዘላለሙን አምላክ የእግዚአብሔርን ስም» እንደጠራ እንመለከታለን። አሁንም የእግዚአብሔርን አዲስ ስም እናገኛለን - ኤል አላም። ይህ ስም ያገለገለው በዚህ ሥፍራ ብቻ ሲሆን፥ የእግዚአብሔርን ዘላለማዊነት ይገልጻል።

18ኛ ጥያቄ፤ - ማር. 9፡50፤ 2ኛ ቆሮ. 13፡11፤ 1ኛ ተሰ. 5፡13 ተመልከት። በእነዚህ ጥቅሶች የታዘዝነው ነገር ምንድነው?

የዚህን ታሪክ ዓላማ ለመረዳት ከባድ ነው። ሙሴ ለማስተማር የሚፈልገው መንፈሳዊ መመሪያ፥ የእግዚአብሔር ልጆች እንደመሆናችን፥ የእግዚአብሔር ልጆች ካልሆኑት ሰዎች ጋር በሰላም ለመኖር መሻት እንዳለብን ነው። እስራኤላውያን ከእስራኤል ምድር ውጭ ከሚኖሩ ሰዎች ጋር ሰላማዊ ቃል ኪዳኖችን መግባት ነበረባቸው። እንደዚሁም ክርስቲያኖችም በሰላም-ወዳድነታቸው መታወቅ አለባቸው። ይህ ማለት እርስ በርሳችን ብቻ በሰላም መኖር አለብን ማለት ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ከሰው ሁሉ ጋር ነው። በሰላም መኖር ማለት በሚያደርጉት ወይም በሚያምኑት ነገር ሁሉ መስማማት አለብን ማለት አይደለም። በተጨማሪ ደግሞ ምስክርነትን እናቆማለን ማለት አይደለም። ሰላም፥ ወንጌልን ለማሠራጨት ጠቃሚ መሣሪያ ሊሆን ይችላል። በክርስቲያኖችና ክርስቲያን ባልሆኑት ሰዎች መካከል ግጭት ቢኖር፥ የግጭቱ መንስዔ ክርስቲያን ካልሆኑት ሰዎች በኩል መምጣት አለበት። የሚያሳዝነው ብዙውን ጊዜ ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸውና

ከሌሎች ጋር በመጣላታቸው የታወቁ ናቸው። በሰላም መኖር የሕይወት መመሪያችን ሊሆን ይገባል። በእርግጥ፥ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች ክርስቲያኖችን የሚያሳድዱባቸው ጊዜያት ይኖራሉ። ዳሩ ግን የቅዱሳት መጽሐፍ ትዕዛዝ «ቢቻላችሁስ፥ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ» (ሮሜ 12፡18) የሚል ነው።

19ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ በክርስቲያኖች መካከል ጠብ ይፈጠራልን? ከሆነ፥ ቤተ ክርስቲያንህ ሰላም ለመፍጠር ምን እያደረገች ነው?

ለ) ለክርስቲያኖች በሰላም መኖር የሚያስቸግረው ለምንድነው?

ሐ) በአንተ ወይም በቤተ ክርስቲያንህና ክርስቲያን ባልሆኑ ሰዎች መካከል ሰላም አለ? ካልሆነ፥ ለምን?

ሦስተኛ ቀን ፡- ዘፍጥረት 22፡1-19

አንድ ጊዜ አንድ ሰው ሲናገር፥ እግዚአብሔር አንድን ሰው መጀመሪያ በደንብ ሳይፈትነው በደንብ አድርጎ የሚጠቀምበት አጋጣሚ እጅግ አናሳ ነው ብሏል። እምነቱ እንዲነጥርና እግዚአብሔርን ለማገልገል እንዲዘጋጅ፥ በመጀመሪያ በመከራ እሳት ውስጥ ያስቀምጠዋል። ከሁሉም በላይ የሚፈለገው ፈተና፥ በምድር ላይ ከምንም ነገር በላይ እግዚአብሔርን የመውደድና ለእርሱም የመታመን ፈተና ነው። አብርሃም ይስሐቅን ለመሠዋት በተነሣ ጊዜ በዚህ ፈተና ውስጥ ነበር ያለፈው። እግዚአብሔር አብርሃምን፥ ይስሐቅን በመሠዋት ለእርሱ መልሶ እንዲሰጠው ጠየቀው።

20ኛ ጥያቄ፤ - በሕይወትህ ያለፍህባቸውንና ከእግዚአብሔር ጋር ባለህ ጉዞ የረዱህን አንዳንድ ፈተናዎች ዘርዝር።

21ኛ ጥያቄ፤ - ዘፍጥረት 22፡1-19 አንብብ። ሀ) እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን ፈተና ግለጽ።

ለ) በቁጥር ሁለት ውስጥ፥ አብርሃም ለይስሐቅ የነበረውን ፍቅር እግዚአብሔር እንደምን አጉልቶ ነው የገለጸው?

ሐ) አብርሃም ወደ ሞሪያ ተራራ ለመድረስ ምን ያህል ጊዜ ወሰደበት?

መ) በቁጥር 5፥ አብርሃም እምነቱን ያሳየው እንዴት ነበር?

ሠ) በቁጥር 8፥ አብርሃም እምነቱን ያሳየው እንዴት ነበር?

ረ) በዚህ ታሪክ ውስጥ ይስሐቅ እምነቱንና ታዛዥነቱን ያሳየው እንዴት ነው?

ሰ) እግዚአብሔር ከአብርሃም መታዘዝ የተረዳው ነገር ምን ነበር?

ሸ) እግዚአብሔር በይስሐቅ ምትክ ለመሥዋዕትነት የሰጠው ነገር ምን ነበር?

ቀ) አብርሃም ለቦታው የሰጠው ስም ምን ነበር?

በ) በተራራው ከአብርሃም ጋር የተገናኘው ማን ነበር? (ቁ. 15)

ተ) እግዚአብሔር ለአብርሃም ምን ምን የተስፋ ቃሎች ሰጠ?

ብዙ ዓመታት ስላለፉ (21፡34)፥ ይስሐቅ ከሕፃንነት ወደ ልጅነት፥ ከልጅነት ወደ ወጣትነት አድጓል። በዘፍጥረት 22 የተጠቀሱት ክስተቶች በተፈጸሙ ጊዜ፥ የይስሐቅ ዕድሜ ምን ያህል እንደነበረ ባናውቅም፥ ምናልባት ከአሥራ አምስት እስከ ሃያ ዓመት ሳይሆን አይቀርም። በነዚያ ዓመታት ውስጥ አብርሃም ለይስሐቅ የነበረው ፍቅር አድጓል። ብቸኛ ልጅ በመሆኑ፥ አብርሃም የሽምግልና ልጁን በጣም ሳይወደው አልቀረም። ስለዚህ ለልጁ የነበረው ፍቅር፥ ለአምላኩ ከነበረው የሚበልጥበት አደገኛ ሁኔታ ነበር። በመሆኑም እግዚአብሔር አብርሃምን «ለመፈተን» ወሰነ።

«መፈተን» የሚለው ቃል ሁለት የተለያዩ ትርጉሞች ሊኖሩት ይችላል። በመጀመሪያ፥ ሰይጣን ክርስቲያኖችን በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት እንዲሠሩ የሚመራበት ክፉ ፈተና ሊሆን ይችላል። ይህ እግዚአብሔር የማያመጣው የፈተና ዓይነት ነው (ያዕ. 1፡13 ተመልከት)። ሁለተኛ፥ የዚህ ቃል ትርጉም፥ በእግዚአብሔር ላይ ያለን

እምነት መፈተን፥ ወይም የመሰጠታችን ማረጋገጫ ሊሆን ይችላል (ዘጸ. 20:20፤ ዘዳ. 8:2 ተመልከት)። የዚህ ዓይነቱ ፈተና እንደ ስደት ከመሳሰሉ ውጫዊ መከራዎች፥ ወይም ለእግዚአብሔር ባለን ታማኝነት ላይ ከሚነሡ ውስጣዊ ትግሎች ሊመጣ ይችላል።

22ኛ ጥያቄ፤ - ለእያንዳንዱ ፈተና ዓይነት ምሳሌ ስጥ።

አንድ ቀን እግዚአብሔር ወደ አብርሃም መጣና ይስሐቅን ወደ ሞሪያ ተራራ በመውሰድ የሚቃጠል መሥዋዕት አድርጎ እንዲሠዋው ጠየቀው። እግዚአብሔር ይስሐቅን እንዴት እንደገለጸው ልብ በል። «የምትወደው፥ አንድ ልጅህ፥ ይስሐቅ» ብሎት ነበር። የእግዚአብሔር ቃል በአብርሃምና በይስሐቅ መካከል የነበረውን የጠለቀ ፍቅር ያሳየናል። በእርግጥ አብርሃም ይህ የእምነቱ መፈተን ብቻ እንደ ነበረና ልጁን መሠዋት እንዳልነበረበት አልተገነዘበም ነበር። ልጁን እንዲሠዋ የተሰጠ ግልጽ የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ስለ ነበረ፥ አንድም እግዚአብሔርን ያለመታዘዝና ይስሐቅን ማዳን፥ አሊያም እግዚአብሔርን መታዘዝና ይስሐቅን መሠዋት እንደነበረበት ያውቅ ነበር።

እግዚአብሔር ለአብርሃም ሌላ ዓይነት ፈተና ያልሰጠውና ይስሐቅን እንዲሠዋ የጠየቀው ለምን ነበረ? ሁለት አበይት ምክንያቶች አሉ። በመጀመሪያ፥ የተስፋው ልጅ የሆነው ይስሐቅ ለአብርሃም እምነት አደገኛ ሆኗል። አብርሃም ለይስሐቅ የነበረው ፍቅር፥ ለእግዚአብሔር ከነበረው ፍርሃት ከሞላ ጎደል እስከሚበልጥበት ደረጃ ላይ ደረሰ። ይስሐቅ የአብርሃም ጣዖት ወደ መሆኑ ሊለወጥ ተቃረበ። ለእግዚአብሔር ካለን ፍቅርና መታዘዝ የምናስቀድመው ማንኛውም ነገር ጣዖት ነው። ይህ ከአብርሃም የእምነት ጉዞ በተቃራኒ ስለ ነጎደ፥ እግዚአብሔር አብርሃምን ከእርሱና ከይስሐቅ አንዱን እንዲመርጥ አስገደደው።

23ኛ ጥያቄ፤ - ዛሬ ለክርስቲያኖች ጣዖት ሊሆኑ የሚችሉ አንዳንድ ነገሮች ምንድናቸው?

ሁለተኛ፥ በጥንቱ ዓለም፥ ሰዎች ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅርና መሰጠት የሚገልጹበት ጉልህ መንገድ፥ ለእነርሱ ከሁሉም በላይ ውድ የሆነውን ነገር ለእርሱ በመሠዋት ነበር። ይህም ልጅን ወደ መሠዋት

መራቸው (2ኛ ነገሥ. 3:27፤ ኤር. 19:5 ተመልከት)። በኋላ እግዚአብሔር በተለይ እስራኤላውያን ልጆቻቸውን እንዳይሰዉ ነግሮአቸዋል (ዘሌ. 18:21)። ሆኖም፥ አብርሃም በዓለም ውስጥ ካለው ከማንኛውም ነገር በላይ እግዚአብሔርን እንደሚወድና እንደሚያከብር ለሁሉም ሰው ማሳየት ነበረበት። ይህንንም ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች ሁሉ በሚረዱበት መንገድ አሳየ። ማንም ባዕድ አምላኪ፥ ልጁን ስለ ሠዋ፥ አብርሃም እውነተኛውን አምላኩን በመውደድ ልጁን ግን ባይሠዋ ከእርሱ በላይ መውደዱን በጉራ መልክ ሊናገር አይችልም።

አብርሃም የተስፋውን ልጅ ለማግኘት ለ25 ረዣዥም ዓመታት ሲጠብቅ ቆይቷል። ይስሐቅ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች እንደሚወርስ ያውቃል። ከዚህ ቀደም ሌላውን ልጁን እስማኤልን አጥቷል። ፈተናውን የከፋ የሚያደርገው ደግሞ፥ እግዚአብሔር ለአብርሃም እርባና የሌለው የሚመስለውን ነገር እንደሚያደርግ ነው። ጥያቄው እርባና የሌለው ቢሆንም እንኳ፥ ፈተናው የቀረበው አብርሃም እስከ ምን ደረጃ ድረስ ለእግዚአብሔር እንደሚታዘዝ ለማየት ነበር። በእርግጥ በመጨረሻ ስለሚሆነው ነገር አብርሃም የሚያውቀው ነገር አልነበረውም።

እግዚአብሔር አብርሃምን ወደ ሞሪያ ተራራ እንዲሄድ ጠየቀው። በዚህ ጊዜ አብርሃም በከነዓን ምድር ደቡባዊ ክልል ይኖር ነበር። የሞሪያ ተራራ የሚገኘው በኢየሩሳሌም ውስጥ ነበር (2ኛ ዜና 3:1)። አሁንም የእግዚአብሔር እጅ በሥራ ላይ እንዳለ እንመለከታለን። ሞሪያ እስራኤላውያን ለበርካታ ክፍለ-ዘመናት እግዚአብሔርን የሚያመልኩበት፥ የወደፊት የሰሎሞን ቤተ መቅደስ ሥፍራ መሆን ነበረበት። በዛሬው ጊዜ ግን በዚህ ሥፍራ ላይ አንድ ትልቅ የሙስሊም መስጊድ ተሠርቶበት ይገኛል። እዚህ ላይ የሚያስገርመው ነገር በመጀመሪያው የአይሁድ ቤተ መቅደስ ላይ በተሠራው በዚህ ‹ደዩም አፍ ዘ ሮክ› ( ) በመባል በሚታወቀው መስጊድ ውስጥ፥ አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት አብርሃም ይስሐቅን ለመሠዋት የሞከረበት ግዙፍ ዓለት የመኖሩ ጉዳይ ነው።

አብርሃም ከውሳኔው ጋር እየታገለ በርካታ ረዣዥም ሰዓታ እንዳሳለፈ የሚያጠራጥር አይደለም። በመጨረሻ ግን ለእግዚአብሔር የነበረው ፍቅርና መታዘዝ አሸነፈ። በቁርጥ ታዛዥነት፥ አብርሃም ለመሄድና ይስሐቅን ለመሠዋት፥ በማለዳ ሁሉንም ዝግጅት አጠናቀቀ። ሙሴ በእርግጥ አብርሃም እግዚአብሔርን እንደሚታዘዝና እንደማይታዘዝ፥ ከታዘዘም የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች እንዴት እንደሚሆኑ፥ ለታሪኩ በርካታ ዝርዝሮች በመስጠት በጉጉት እንድንከታተለው ያደርገናል። ወደ ተራራው አቅራቢያ እስኪደርሱ ድረስ ለሦስት ቀናት ተጓዙ። በዚያም ባሪያዎቹን እንዲቆዩ ነገራቸው። ምናልባት ልጁን ሲሠዋ እንዳያዩ ወይም ለመከላከል እንዳይሞክሩ ፈልጎ ይሆናል።

አብርሃም በእግዚአብሔር ላይ ስለ ነበረው እምነት ሁለት ፍንጮች ተሰጥቶናል። በመጀመሪያ፥ አብርሃም ለሎሌዎቹ፡- «እኔና ልጄ ወደዚያ ሂደን እንሰግዳለን፤ ወደናንተም እንመለሳለን» ብሏል። እንዴት እንደሚሆን ባያውቅም፥ በይስሐቅ በኩል የተስፋ ቃሎቹ በሙሉ እንደሚፈጸሙ ያውቅ ነበር። ለተስፋ ቃሎቹ መፈጸም ይስሐቅ በሕይወት መኖር ነበረበት። ስለሆነም አብርሃም እንደሚመለሱ ከሞላ ጎደል ያውቅ ነበር። ከሞት በተነሣው አምላክ ላይ የነበረው እምነቱ ዛሬ ለእኛ ትልቅ አርአያ ነው።

ሁለተኛ፥ ይስሐቅ «በጉ የታለ?» ባለው ጊዜ፥ አብርሃም «የመሥዋዕቱን በግ እግዚአብሔር ያዘጋጃል» በማለት መለሰለት። አብርሃም ግራ በሚያጋባና ልብን በሚያውክ ሁኔታ ውስጥ እግዚአብሔርን ተማመነ። እግዚአብሔር በይስሐቅ በኩል እንደሚባርከው ተስፋ ሰጥቶታል። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር የሰጠውን ያንኑ ልጅ እንዲሠዋ ተጠይቋል። ይህ ለአብርሃም ሊገባው አልቻለም። ዳሩ ግን እግዚአብሔርን በመተማመን ታዘዘ።

ወደ ተራራውም በደረሱ ጊዜ፥ አብርሃም ይስሐቅን ለመሠዋት ሽር ጉድ ይል ጀመር። ዳሩ ግን ይስሐቅን ለማረድ፥ ቢላዋውን ባነሣ ጊዜ እግዚአብሔር ከለከለው። አብርሃም በአእምሮው ይስሐቅን ቀደም ብሎ ሠውቷል። እግዚአብሔር የአብርሃምን ፍቅር እንጂ፥ የይስሐቅን ሞት አልፈለገም ነበር። አሁን ፈተናው አበቃ። እግዚአብሔርም ‹አንድ

ልጅህን ለእኔ አልከለከልህምና እግዚአብሔርን የምትፈራ እንደሆንህ አሁን አውቄአለሁ› አለ።

24ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) እግዚአብሔርን «መፍራት» ማለት ምን ማለት ነው?

ለ) ይህ በሕይወትህ የታየው እንዴት ነው?

«እግዚአብሔርን መፍራት» እግዚአብሔር ከልጆቹ የሚፈልገው ባሕርይ ነው። ይህም እግዚአብሔርን ማክበርና ከፍ ከፍ ማድረግ፥ ሁል ጊዜም ኃይሉንና ግርማውን ማወቅ ማለት ነው። እርሱን ጌታችንና አለቃችን አድርገን ሕይወታችንን ሁሉ ለእርሱ ማስገዛት ማለት ነው። እኛ ክርስቲያኖች አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔርን ፍቅር በጣም እያጋነንን፥ እግዚአብሔር ታላቅና የሚያስፈራ አምላክ መሆኑን ግን እንዘነጋለን። አምልኮ ለክርስቲያን የፍቅርና የፍርሃት ውህደት ነው። እግዚአብሔርን ስለምንወድ፥ ይህ ወደ እርሱ እንድንመጣና እንድናመልከው ድፍረት ይሰጠናል። ዳሩ ግን ከታላቅነቱና ከኃይሉ የተነሣ፥ የተቀደሰ ፈርሃ-እግዚአብሔርም ሊኖረን ይገባል። ከእነዚህ መካከል አንዱ በሚጎድልበት ጊዜ፥ አምልኮአችን ሚዛናዊነትን ያጣል። እግዚአብሔርን እየወደድን ሳንፈራው ስንቀር፥ እግዚአብሔርን ቀለል አድርገን እናየዋለን። ወይም እግዚአብሔርን ስንፈራውና ከእርሱ ዘንድ ፍቅርና ተቀባይነት እንደ ሌለን ስንቆጥር፥ ወደ «ጸጋ ዙፋኑ» ለመቅረብ አንደፍርም (ዕብ. 4፡16)። ይህ አንዳንድ ሰዎች እንደ ማሪያምና መላእክት በመሳሰሉ አማላጆች በኩል እንዲጸልዩ አድርጎአቸዋል።

አብርሃም የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰምቶ ወደ ላይ ተመለከተ። በዚያም በሐረግ የተያዘ በግ ተመለከተ። እግዚአብሔር እንዳዘጋጀለት በመረዳት፥ በጉን ወሰደውና ሠዋው። አብርሃምም ቦታውን «እግዚአብሔር ያዘጋጃል» ብሎ ጠራው። አሁንም ለእግዚአብሔር ሌላ ስም እንደሰጠው እናያለን - ያህዌ ይርኤ። አብርሃም እግዚአብሔር በግ እንደ ሰጠው ብቻ ሳይሆን፥ እርሱን እስከታዘዘ ድረስ ሁል ጊዜም ሁሉን ነገር እንደሚሰጥ አሁን አወቀ። አብርሃም ተራራውን በመሰየም፥ ትውልዱ ሁሉ የሚያመልኩትን የእግዚአብሔርን ባሕርይ የሚያስታውስ የተቀደሰ ሥፍራ እያዘጋጀላቸው ነበር። በቁጥር 8 ላይ

አብርሃም ለይስሐቅ ተስፋ እንደሰጠው፥ እግዚአብሔር ለመሥዋዕቱ የሚያስፈልገውን ነገር አዘጋጀላቸው።

25ኛ ጥያቄ፤ - ይህ የእግዚአብሔር ባሕርይ ዛሬ ለእኛ ማበረታቻ የሚሆነን እንዴት ነው?

አብርሃም ለሁለተኛ ጊዜ ከ «እግዚአብሔር መልአክ ጋር» ተገናኘ። አሁንም በእግዚአብሔርና በመልአኩ መካከል ያለውን የቀረበ ግንኙነት ልብ በል። አብርሃምን የጠራው እግዚአብሔር ነበር (ቁ. 11)። አሁን አብርሃምን የጠራው የእግዚአብሔር መልአክ ነበር (ቁ. 15)። እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር የገባቸውን ቀደምት የተስፋ ቃሎች አደሳቸው። ዳሩ ግን አንዳንድ መጠነኛ ልዩነቶች አሉ። እግዚአብሔር ለመጀመሪያ ጊዜ «በራሴ ማልሁ» በሚል መሀላ ላይ የተመሠረቱ የተስፋ ቃሎች ሰጠ። እንዲሁም ዘሮቹ በሕዝብች ላይ ድልን እንደሚቀዳጁና የጠላቶቻቸውን ከተሞች እንደሚወርሱ ተናገረ። ይህ ወደ ተስፋዪቱ ምድር ሊገቡና በኢያሱ መሪነት ከጠላቶቻቸው ጋር ሊዋጉ ለነበሩት እስራኤላውያን፥ ምን ያህል የሚያበረታታ የተስፋ ቃል መሆን አለበት!

ምንም እንኳ በታሪኩ ውስጥ ባይጠቀስም፥ ይስሐቅም እምነቱን አሳይቷል። በዚህ ጊዜ ይስሐቅ 16 ዓመታት ገደማ የሚሆነው ወጣት ነበር። ከ100 ዓመት በላይ የሆነውን አረጋዊ አባቱን ላለመታዘዝና ላለመሠዋት ሊታገል ይችል ነበር። ለመሠዋት በመሠውያው ላይ በሚያጋድመው ጊዜ አሻፈረኝ ማለት ይችል ነበር። ይስሐቅ የእግዚአብሔርን መንገድ ለሚከተሉት፥ ለወላጆች በተገዢነት የመታዘዝ መልካም ምሳሌ ነው።

26ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) አብርሃም ይስሐቅን ለመሠዋት ባቀረበበት ሁኔታና በኢየሱስ ሞት መካከል ያሉትን ተመሳሳይ ነገሮች ዘርዝር።

ለ) የአብርሃም መሥዋዕት ከእግዚአብሔር አብ ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

ሐ) የይስሐቅ ሁኔታ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ካደረጋቸው ነገሮች ጋር እንዴት ይመሳሰላል?

የአብርሃም ይስሐቅን መሠዋት፥ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ከቀረቡት እጅግ ግልጽ መግለጫዎች አንዱ ነው። አብርሃም አንድ ልጁን ለመሠዋት እንደወሰደ ሁሉ፥ እንደዚሁም እግዚአብሔር አብ አንድያ ልጁን በመስቀል ላይ እንዲሞት ላከው። ከሁሉም የሚልቀው ልዩነት፥ እግዚአብሔር ለአብርሃም በልጁ ፋንታ የሚሠዋውን ምትክ ሲሰጠው፥ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ለኢየሱስ የቀረበ ምትክ አለመኖሩ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ መሠረት ሞቷል። ጳውሎስ «ለገዛ ልጁ ያልራራለት ነገር ግን ስለ ሁላችን አሳልፎ የሰጠው ያው ከእርሱ ጋር ደግሞ ሁሉን ነገር እንዲያው እንዴት አይሰጠንም?» (ሮሜ 8፡32) በማለት የተናገረው ይህን ታሪክ እያሰበ መሆኑ አያጠራጥርም። የኃጢአት ይቅርታ እንድናገኝ፥ የእግዚአብሔር ቤተሰብ እንድንሆንና ለዘላለም ከእርሱ ጋር እንድንኖር፥ የስጦታዎች ሁሉ ምንጭ የሆነው ያህዌ ይርኤ፥ ልጁን ሰጠን።

ይህ ታሪክ ለእስራኤላውያን አስፈላጊ ትምህርት መሆን ነበረበት። እግዚአብሔር ወደ በረሃ እንዲሄዱ፥ ቀይ ባሕርን እንዲያቋርጡ፥ ወዘተ. የመሳሰሉ፥ የማይሞከሩ የሚመስሉ በርካታ ትዕዛዛት እንዲታዘዙ ይጠይቃቸው ነበር። እግዚአብሔር ታማኝነታቸውንና ታዛዥነታቸውን ይፈልግ ነበር። እርሱም በበኩሉ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ እንደሚሰጣቸው ተስፋ ሰጠ።

አብርሃም ይስሐቅን የመሠዋቱ ሂደት፥ እግዚአብሔር ከእኛ ምን እንደሚፈልግ ከሚያሳዩ እጅግ ግልጽ መግለጫዎች አንዱ ነው። ምንም እንኳ እግዚአብሔር፥ አብርሃም ይስሐቅን እንዲሠዋው ቢጠይቀውም፥ የተፈጸመው እውነተኛ ነገር አብርሃም እራሱን ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር መሠዋቱ ነበር። ፈቃዱን፥ መሻቱን፥ ጥበቡን፥ እና እቅዱን ለእግዚአብሔር ሰጠ። እኛም የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች የምንሆን ከሆነ፥ ማንኛውንም ነገር ለእግዚአብሔር ከመስጠት ወደ ኋላ አንመለስም። ለእኛ ትርጉም ባይሰጠን እንኳ፥ እግዚአብሔር የሚያዝዘንን ነገር ሁሉ ሙሉ ለሙሉ መፈጸም አለብን። መጽሐፍ ቅዱስ ራሳችንን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርገን እንድናቀርብ ይጠይቃል (ሮሜ 12፡1)።

ኢየሱስ በሉቃስ 14፡26፥ «ማንም ወደ እኔ የሚመጣ ቢኖር አባቱንና እናቱን ሚስቱንም ልጆቹንም ወንድሞቹንም እህቶቹንም የራሱንም ሕይወት ስንኳ ሳይቀር ባይጠላ፥ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም» ብሏል። እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን ያንኑ ፈተና በእያንዳንዳችን ፊት ያስቀምጣል። እግዚአብሔርን ከምንም ነገር በላይ እንወደዋለን? ትክክለኛ ነገር በማይመስለን፥ ወይም በእቅዳችን መሠረት የማይከናወን ቢሆንም እንኳ፥ እርሱን ለመታዘዝ እንፈቅዳለን? እግዚአብሔር የማንፈልገውን፥ ወይም የማንጠነቀቅለትን ነገር፥ ለእርሱ እንድንሰጠው አይጠይቅም። እግዚአብሔር ከእኛ የሚሻው ከሁሉ የተሻለውን ነገራችንን ነው። እግዚአብሔር ሙሉ ታማኝነታችንን ይፈልጋል። እንድንወደውና ሙሉ ለሙሉ እንድንፈራው ይፈልጋል። በእርግጥ እግዚአብሔርን ለመከተል የምንፈልግ ከሆንን፥ ለእኛ ከሁሉም በላይ ውድና አስፈላጊ የሆነውን ነገር ለመሠዋት ፈቅደኞች መሆን አለብን።

27ኛ ጥያቄ፤ ሮሜ 12፡1 አንብብ።

ሀ) እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው ምን ዓይነት መሥዋዕት ነው?

ለ) በሕይወትህ ውስጥ ለእግዚአብሔር ሙሉ ለሙሉ ያልሠዋሃቸው አንዳንድ ነገሮች ምንድናቸው? ሕይወትህን «ሕያው መሥዋዕት» አድርገህ ለማቅረብ አሁኑኑ ጊዜ ውሰድ። ለእርሱ በታዛዥነት ማስገዛት የሚያስፈልጉህን የሕይወት ክፍሎች እንዲያሳይህ እግዚአብሔርን ጠይቅ።

ይህ ለአንተ ከባድ ይመስልሃል? እግዚአብሔር ሁሉን የሚሰጥ ያህዌ ይርኤ እንደሆነ አስታውስ። ሕይወትህን በእርሱ ላይ ለማስደገፍ የምትችልበትን ብቃት ሳይቀር፥ ሁሉንም ነገር ሊሰጥህ የተስፋ ቃል ይገባልሃል።

አራተኛ ቀን፡- ዘፍጥረት 22፡20-24፤ 23

ዘፍጥረት 22 የአብርሃም ሕይወት ዋነኛው ታሪክ ነው። የእምነት ሰው የሆነው አብርሃም፥ በአንድ የማጠቃለያ ፈተና እግዚአብሔርን ከምንም ነገር በላይ እንደሚወድ አስመስክሯል። ከዘፍጥረት 22፡20 እስከ 23 ያለው፥ በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ የሽግግር ክፍል ነው። ታሪኩ ከአብርሃም ወደ ልጁ ይስሐቅ መለወጥ ይጀምራል። የመጀመሪያው የእምነት አባት ሞቶ፥ ሁለተኛው ትውልድ ሥፍራውን ለመተካት ይነሣል።

28ኛ ጥያቄ፤ - ዘፍ. 22፡20-24፥ ዘፍ. 23 አንብብ።

ሀ) በዚህ ሥፍራ የተጠቀሱት የናኮር ልጆች ስንት ናቸው?

ለ) ሙሴ ዘፍ. 22፡20-24ን የጨመረው ለምን ይመስልሃል?

ሐ) ሣራ በሞተች ጊዜ ስንት ዓመቷ ነበር?

መ) በ23፡4 አብርሃም ራሱን የሚገልጸው እንዴት ነው?

ሠ) አብርሃም ከኬጢያውያን ዘንድ መሬቱን ሊገዛ የፈለገው ለምን ነበር?

ረ) አብርሃም ሣራን በሰው መቃብር ለመቅበር ወይም መሬቱን በነጻ ለመቀበል ያልፈለገው ለምን ይመስልሃል?

1. የናኮር ልጆች ዝርዝር (22፡20-24)

ሦራ ሦስት ልጆች እንደነበሩት ከዘፍጥረት 11 ጥናታችን ታስታውሳለህ። ሐራን የተባለው አንዱ ልጅ ሞቷል። እኛም የታራ ሁለተኛ ልጅ የሆነውን የአብርሃም ሕይወት እያጠናን ነው። ዳሩ ግን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሦስተኛው ልጅ፥ ናኮር የዘገበው በጣም ትንሽ ነው።

ናኮር ከአብርሃም ጋር ወደ ተስፋዱቱ ምድር አልሄደም። በኋላ ግን ያዕቆብ ከናኮር የልጅ ልጅ ጋር ለመኖር ወደ ሐራን ሄዷል (ዘፍ. 29፡4-5)። በዘፍጥረት 22፡20 ከተወሰኑ ጊዜያት በኋላ አብርሃም የወንድሙን ወሬ እንደሰማ ይናገራል። ይህ ከይስሐቅ መወለድ በፊት የሆነ አይመስልም። ይልቁንም ለጥቂት ጊዜ በከነዓን ምድር ሲኖር ሳለ ነበር። ናኮርና ሚልካ በበርካታ ልጆች ተባርከው ነበር።

ናኮር 12 ልጆች ነበሩት። ስምንቱ የተወለዱት ከሚስቱ ከሚልካ ሲሆን፥ አራቱ ከቁባቱ የተገኙ ነበሩ። በዘፍጥረት ውስጥ ቁልፍ ከሆኑት ሰዎች ምን ያህሉ 12 ልጆች እንደነበሯቸው መመልከቱ አስገራሚ ነገር ነው። ናኮር 12 ልጆች ነበሩት። እስማኤል 12 ልጆች ነበሩት። ያዕቆብም 12 ልጆች ይኖሩታል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ 12 ቁጥር ብዙውን ጊዜ የሙሉነት ምልክት ነው።

ዳሩ ግን ትኩረት የተሰጠው፥ በኋላ የይስሐቅ ሚስት የምትሆነው የርብቃ አባት በነበረው በባቱኤል ላይ ነው (ምዕራፍ 24)። አሁን ይስሐቅ ሚስቱን ከየት እንደሚያገኝ ፍንጭ ተሰጥቶናል።

2. የሣራ ሞትና ቀብር (23፡1-20)

በአብርሃም ሕይወት ውስጥ ብዙ ጊዜ አለፈ። በመጨረሻም ሣራ በ127 ዓመት ዕድሜዋ ሞተች። ይህም በእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች ላይ አዲስ ችግር አስከተለ። እናት ሞታ ሳለች፥ የምድሪቱና የትውልዶች የተስፋ ቃሎች እንዴት ይፈጸማሉ? ይህ እንግዲህ የቀደሙት የእምነት አባቶች እግዚአብሔር ለእነርሱ የገባላቸውን የተስፋ ቃሎች ሳያገኙ መሞት ጀመሩ ማለት ነው። የሣራ ሞት የአርሱም ሞት ከደጅ እንደቀረበ ለአብርሃም የሚያስታውስ ክስተት ነበር። አብርሃም ለሣራ ሊያለቅስላትና ሊቀብራት ወደ ወገኖቹ ምድር ሊመለስ ይገባው ነበር። ዳሩ ግን የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች ፍጻሜ የተመለከተው በመጠኑ ቢሆንም፥ የአብርሃም እምነት እስከ መጨረሻው ድረስ ጸና።

በአብርሃም ዘመን አንድ ሰው የሚቀበርበት ሥፍራ ትልቅ ክብር የሚሰጠው ነበር። ቢቻል ደግሞ፥ ለቀብር ወደ ትውልድ ሥፍራቸው ይወስዱ ነበር። በአንድ በኩል፥ በዘፍጥረት 22 መጨረሻ ላይ የናኮር መጠቀስ፥ የአብርሃም ቤተሰቦች በትውልድ አገራቸው ስኬታማ ሕይወት ይመሩ እንደነበር ለመግለጽ ነው። አብርሃም የሣራን አስከሬን ለመቅበር ወደዚያ ይዞ ሊሄድና የተስፋዱቱ ምድር የነበረችውን ከነዓንን ሊተው ይገባው ነበር? አስከሬንን ከቀብር በፊት ለብዙ ዓመታት ለማቆየት የሚቻልባቸው መንገዶች፥ በተለይም በግብፃውያን ዘንድ ይታወቁ ነበር። ዳሩ ግን አብርሃም ቤተሰቡ ወደ ነበረበት ወደ ትውልድ አገሩ የመመለስ ፍላጎት እንዳልነበረው ግልጽ ነው። ይልቁንም አሁን

አዲሱ መኖሪያው ከነዓን እንደነበር ለሁሉም ሰው አስታወቀ። የቀብር ቦታ መግዛቱም፥ አብርሃም ወደ አገሩ ለመሄድ እንዳልፈለገ የሚያመለክት ነው።

የአብርሃም ከኬጢያዊው ኤፍሮን የመቃብር ሥፍራ የመግዛቱ ታሪክ፥ ለጥንቱ ሰዎች ሕጋዊ የመገበያየት ሥርዓት ምሳሌ ነው። አብርሃም በኬጢያውያን (የከነዓናውያን ሌላው መጠሪያቸው ነው) መካከል ይኖር ነበር። ሕይወቱን እንደ «እንግዳና መጻተኛ» አድርጎ ገልጾአል። ከዚህም የተነሣ አስክሬኑን የሚቀብርበት ሥፍራ አለነበረውም። በዚህ አብርሃም ምድርና መብት እንዳልነበረው እያሳየ ነበር። የዕብራውያን መልዕክት በእግዚአብሔር የተሠራችውን ዘላለማዊት ከተማ እየተጠባበቀ እንደነበር ይናገራል (ዕብ. 11፡8-16)።

አብርሃም የቀብር ሥፍራን በተመለከተ ወደ ኬጢያውያን መሪዎች በቀረበ ጊዜ፥ በመጀመሪያ ሣራን ከመቃብሮቹ በአንዱ መቅበር እንደሚችል ገለጹለት። አብርሃም ሣራን በእነርሱ መቃብር ውስጥ ለመቅበር ለምን እንዳልፈለገ አናውቅም። ሣራ በመቃብሩ እንኳን ከአሕዛቦች እንደ አንዱ እንዳትሆን በመስጋቱ እንደሆነ አይመስልም። ምናልባት ሌሎች ሦስት ምክንያቶች ነበሩ። በመጀመሪያ፥ የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝብ እንደ መሆኑ በቤተሰቡና ሊጠፉ በነበሩት ከነዓናውያን መካከል የነበረውን ልዩነት እንዳለ ለማቆየት ሳይፈልግ አይቀርም። ከነዓናዊ እንዳልሆነና ከእነርሱም ጋር ሊተባበር እንደማይፈልግ ሁሉም ሰው እንዲገነዘብ ፈለገ። ሁለተኛ፥ ከነዓናውያን በእርሱ ላይ የሚመጻደቁበት ምንም ውለታ እንዲውሉለት አልፈለገም ነበር። ሣራን በመቃብራቸው ውስጥ ቢቀብራት ኖሮ፥ ሁል ጊዜም «ሚስትህን ስለ ቀበርን እርዳን» እያሉ ከትከሻው አልወርድ ብለው ያስቸግሩት ነበር። ሦስተኛ፥ ምናልባት አብርሃም በከነዓን ምድር ውስጥ ትንሽ የመቃብር ሥፍራ እንዲኖረው የፈለገው፥ በኋላ ዘሮቹ ምድሪቱን በሙሉ እንደሚወርሱ ምልክት እንዲሆን ሊሆን ይችላል።

አብርሃም የኬጢያውያንን መቃብሮች ለመጠቀም አልፈለገም ነበር። ሽማግሌዎች አማላጅ እንዲሆኑለትና ኬጢያዊው ኤፍርን የመቃብር ሥፍራ እንዲሸጥለት ጠየቀ። አብርሃም ይህን በሽማግሌዎቹ ፊት

የጠየቀው፥ በእርሱና በኤፍሮን መካከል ለተፈጸመው ግብይት ሕጋዊ ምስክሮች እንዲሆኑ ነበር። ኤፍሮን ለይስሙላ ያህል አብርሃም ከጠየቀው በላይ መሬትና ዋሻ ሊለግሰው ሞከረ። በኬጢያውያን ሕግጋት መሠረት፥ አንድ ሰው ሰፊ መሬት ቢገዛ ወይም ቢቀበል፥ የመሬት ግብር እንዲከፍልና ከሕዝቡም ጋር በማህበራዊ ግንኙነቶች ውስጥ እንዲሳተፍ ይገደድ ነበር። ዳሩ ግን አንድ ሰው ትንሽ የመሬት ክፍል ብቻ ከኖረው፥ የመጀመሪያው ባለ ርስት፥ ለመንግሥት የሚፈለገውን የመሬት ግብር በመክፈል ከመቀጠሉም በላይ፥ የማህበራዊ ግዴታዎችንም ያሟላል። ምንም እንኳ አብርሃም ከሕጋዊ የገንዘብና የማህበራዊ ግዴታዎች ጋር ሊተሳሰር ባይፈልግም፥ መሬቱን ለመግዛት ተገደደ። አብርሃም የአንድ ኬጢያዊ ዕዳ እንዲኖርበት አልፈለገም ነበር። መሬቱን በ400 የብር ሰቅል ገዛ። ይህም ለትንሽ ቁራሽ መሬት ውድ ዋጋ ነበር። ኤፍሮን በአብርሃም ሐዘንና የቀብር ሥፍራ ማጣት ምክንያት አተረፈ። አብርሃምም በመከራከር ፈንታ፥ የተጠየቀውን ከፈለ። ሕጋዊ የሽያጭና ግዢ ስምምነቶች በሚፈጸሙበት በከተማዪቱ አደባባይ በሕዝብ ሁሉ ፊት፥ አብርሃም ምድሪቱን ገዛ። ይህች በከነዓን ምድር የአብርሃም ንብረት የሆነች ብቸኛ ምድር ነበረች። የቀረው ሁሉ በተስፋ የእርሱ ቢሆንም፥ ዳሩ ግን ገና ከእጁ አልገባም ነበር።

29ኛ ጥያቄ፤- የዚህ ታሪክ አቢይ አስተምህሮ ምን ይመስልሃል?

ይህ የመጀመሪያው አነስተኛ የመሬት ክፍል፥ በእምነት አባቶች ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ሚና ይጫወት ነበር። በመጀመሪያ ሣራ፥ ቀጥሎ አብርሃም፥ ርብቃ፥ ይስሐቅና ያዕቆብ በሙሉ በዚያ ተቀበሩ።

የዚህን ታሪክ አቢይ ትምህርት ለይቶ ማውጣት አስቸጋሪ ነው። ምናልባት ሙሴ የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች በሥጋዊ ሕይወት የተወሰኑ እንዳልሆኑ ለማስተማር ሳይፈልግ አይቀርም። አብርሃም የተስፋ ቃሎቹን ሥጋዊ አፈጻጸም አልተመለከተም። ዳሩግ ግን በሞቱ ለተስፋ ቃሎቹ መንፈሳዊ አፈጻጸም ዋስትና ተሰጥቶታል። አብርሃም መሬቱን በገዛ ጊዜ፥ ወደ ፊት አንድ ቀን፥ የከነዓን ምድር በሙሉ ለዘሮቹ እንደምትሆን በማመን ነበር። ምንም እንኳ የምድሪቱን የተስፋ ቃል በሕይወት ሳሉ ባይቀበሉም፥ በሞታቸው ተስፋው የእነርሱ ነበር።

እንዲሁም አብርሃም ወደ አባቶቹ ምድር ለመመለስ ባለመፈለግ እምነቱን አሳይቷል።

30ኛ ጥያቄ፤- ይህ ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰፋ ቃሎችን ከሚቀበሉበት ሁኔታ ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

እግዚአብሔር ከሚሰጠን የተስፋ ቃሎች በርካታዎቹ በዚህ ሕይወት ውስጥ አይፈጸሙም። ለክርስቲያን ብዙዎቹ የተስፋ ቃሎች የሚሟሉት ከሞት ወዲያ ነው። የሞት ጊዜ ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ላይ እምነት ሊኖራቸው የሚገባበት ጊዜ ነው። ለእነርሱ በሞታቸውም የተስፋ ቃሎቹ የእነርሱ እንዲሆኑ የሚያረጋግጡበት እንጂ፥ የለቅሶ ጊዜ ሊሆን አይገባም። ለምን? ምክንያቱም የሙታን ትንሣኤ ከእኛ ስለማይወሰዱት የዘላለም በረከቶች እርግጠኞች ስለሚያደርገን ነው።

31ኛ ጥያቄ፤- ከዚህ ታሪክ ውስጥ የምንማራቸውንና ከሕይወታችን ጋር የምናዛምዳቸውን አንዳንድ ትምህርቶች ዘርዝር።

አምስተኛ ቀን፡- የዚህን ሳምነት ትምህርት ከልስና ለሳምንታዊ ስብሰባ ለመዘጋጀት፥ የውይይት ጥያቄዎችን ተመልከት።

ሳምንታዊ ስብሰባ

1. ሳምንታዊ የአምልኮ ጊዜ
2. የጸሎት ጊዜ
3. የትምህርቱ ክለሳ
4. የውይይት ጊዜ

ሀ. 1) አብርሃም በእምነት ጉዞው ይበልጥ የታገለው ከየትኞቹ የሕይወት ገጽታዎቹ ጋር ነበር?

2) ዛሬ ክርስቲያኖች የሚታገሉዋቸው አንዳንድ የሕይወት ክፍሎች የትኞቹ ናቸው?

3) የተለያዩ ደካማ የሕይወት ገጽታዎችን ስለማሸነፍ፥ ክርስቲያኖችን ምን ለማስተማር ትችላለህ?

ለ. 1) የአንድ ነብይ አቢይ ሚና ምንድነው?

2) አብርሃም ይህንን ያሚላው እንዴት ነው?

3) የአንድ ካህን አቢይ ሚና ምንድነው?

4) አብርሃም ይህንን ያሚላው እንዴት ነው?

5) ዛሬ እነዚህን ሁለት ሚናዎች በአብያተ ክርስቲያናታችን ውስጥ ለማሚላት የምንችለው እንዴት ነው?

ሐ. 1) እግዚአብሔር አጋርንና እስማኤልን እንዲያባርር ለአብርሃም የነገረው ለምንድነው?

2) መልካም ቢሆኑም እንኳ፥ ክርስቲያኖች ከሕይወታቸው ሊያስወግዱ የሚገባቸው አንዳንድ ነገሮች ምንድናቸው? ለምን?

መ. 1) ክርስቲያኖችና ክርስቲያን ካልሆኑ ሰዎች ጋር በሰላም መኖር የሚያስቸግረው ለምንድነው?

2) በቤተ ክርስቲያንህ በክርስቲያኖች መካከል ጠብ አለ? ለምን?

3) ቤተ ክርስቲያንህ ሰላምን ለመጠበቅ ምን እያደረገች ነው?

4) ቤተ ክርስቲያን ክርስቲያን ካልሆኑ ጎረቤቶች ጋር ያላት ግንኙነት ምን ዓይነት ነው?

5) ያንን ግንኙነት ለማሻሻል ምን ማድረግ ትችላለህ?

ሠ. 1) የአብርሃም ይስሐቅን መሠዋት፥ ለኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔር መሠዋት ተምሳሌት የሚሆነው እንዴት ነው?


2) እግዚአብሔር ከሕይወታችን ለሚፈልገውስ ነገር እንዴት ተምሳሌት ይሆናል?


ረ. ሉቃ. 14፡26ን አንብብ። 1) ይህ ማለት ምን ማለት ነው?

2) ይህ ጥቅስ ከክርስቲያኖች ሕይወት ጋር ሊዛመድ የሚችለው እንዴት ነው? ምሳሌዎችን ስጥ።

3) ክርስቲያኖች ያሏቸው አንዳንድ ጣዖታት ምንድናቸው?

5. ጸሎት።


N
ትንሹ እስያ
የአርመን አገር
የአራራት ተራራዎች
የካስፒየን ባሕር
የካስፒየን ተራራዎች
ካራን
ነነዌ
አሶር
በሁለት ወንዝ መካከል
ሶርያ
ደማስቆ
ፊንቄ
ቆጵርስ ደሴት
ታላቁ ባሕር
የአርሞንዔም ተራራ
ከነዓን
ኢየሩሳሌም
አዜብ (ኔጌብ)
ጌሚም
ግብፅ
የሲና ተራራ
የአባይ ወንዝ
የኤርትራ ባሕር
የቀይ ባሕር
የአካባ ባሕር
የዓረብ ምድረ በዳ
ባቢሎን
የከለዳውያን አገር
ሚዶን
ዑር
የፋርስ ባሕር
ኤፍራጥስ ወንዝ
ጤግሮስ ወንዝ
ዒላም
የዛግሮስ ተራራዎች
ፎኒኛ ካርታ
በብሉይ ኪዳን ጊዜ
የታወቀው ዓለም


2ኛ ካርታ
ከነዓን
N
የአርሞንዔም ተራራ
የሚሮም ውኃ
ፈንቄ
ገሊላ
የገሊላ ባሕር
የቀርሜሎስ ተራራ
ታላቁ ባሕር
ሚሮን
ደብረ ታቦር
የገልዓድ ተራራ
የጊልቦዓም ተራራ
ዶታይን
የጌባል ተራራ
ሴኬም
ኤንኤል
ሰማርያ
ቤቴል
የዮርዳኖስ ሸለቆ
የፍልስጥኤማውያን አገር
የዓረብ ምድረ በዳ
ኢየሩሳሌም
ኤፍራታም
ይሁዳ
የጨው ባሕር
ኬብሮን
ቤርሳቤህ
ተራራዎች
ምድያም
ኤዶም
0 10 20 30 40 50
ኪሎሜትር